ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ETHIOPIAN PUBLIC

# የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምላሽና ቀጣይ እርምጃዎች

# የጤና ሚኒስቴር ሪፖርትና ምክረ ሃሳብ ሰነድ

# ለተከበረው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

# መስከረም 2013 ዓ.ም

---

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት**

በተከበረው ምክር ቤት ፊት ቀርቤ ይህንን የጤና ሚኒስቴር የኮሮና ወረርሽኝ አገራዊ ምላሽ፣ አሁን ያለበትን እንዲሁም ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫና ምክረ ሀሳብ የሚያሣይ ሪፖርት እንዳቀርብ እድሉን ስላገኘሁ በራሴ እና በጤና ሚኒስቴር ስም አመሰግናለሁ፡፡

## መግቢያ

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ለመጀመሪያ ደረጃ በቻይና ከታየበት ጊዜ አንስቶ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ሁሉም ክፍለ አህጉራት በመሰራጨት በዓለማቀፍ ደረጃ ከ200 በሚበልጡ ሀገራት ላይ ተከስቶ ወደ 29 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን በማጥቃት ከዘጠኝ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሰዎች በላይ ለሞት ዳርጓል፡፡ እስከሁን ድረስም ከታማሚዎች ውስጥ 72% ገደማ ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን ቀሪዎቹ አሁንም ቢሆን ከበሽታው ያላገገሙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ወደ 1% የሚሆኑት በፀና የታመሙ ናቸው፡፡

በአፍሪካ አህጉር የወረርሽኙ ሥርጭት በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች ከታየው አንጻር ሲታይ ዝግ ያለ የስርጭት ፍጥነት ሲኖር እስከአሁን በሌላው አለም ላይ ካስከተለውም ሞት አኳያ በንጽጽር የቀነሰ ነው፡፡ ለዚህም እንደምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በአፍሪካ ያለው የህፃናት እና ወጣቶች ብዛት አንዱ ሲሆን (በአፍሪካ አማካኝ እድሜ 19.7 ነው) በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ባለው የምርመራ እና ቅኝት ብቃት ከሌላው ዓለም አንጻር ዝቅተኛ በመሆኑ የታማሚዎችን

ብዛት በትክክል ለመለየት እንቅፋት በመሆኑ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም በአፍሪካ ወረርሽኙ በ57 ሀገራት ላይ ተከስቶ ከ 1.3 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በበሽታው የተጠቁ ሲሆን ከ32 ሺህ በላይ ሰዎች ደግሞ በበሽታው ምክንያት ለሞት ተዳርገዋል፡፡ እስከአሁን ድረስም በበሽታው ከተያዙት ውስጥ ወደ 81% የሚሆኑት ያገገሙ ሲሆን የተቀሩት አሁንም ከበሽታው ያላገገሙ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ 0.7% የሚሆኑት በፀና የታመሙ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር ሀገራችን በምትገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ውስጥም በየእለቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በበሽታው እየተጠቁ ሲሆን እስከ አሁንም ከ150 ሺህ በላይ ሰዎች በበሽታው የተጠቁ ሲሆን ከ2900 በላይ ሰዎችም ለሞት ተዳርገዋል፡፡ እስከአሁን ድረስም በበሽታው ከተያዙት ውስጥ ወደ 55 % የሚሆኑት አገግመዋል፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ (66ሺ) እና ኬንያ (36 ሺ) በላይ ታማሚዎችን ያሏቸው ሲሆን ይህም ደግሞ ከቀጠናው ከፍተኛ የታማሚዎችን ቁጥር ያስመዘገቡ ሀገራት ያደርጋቸዋል፡፡

በሽታው ከጤናም ባለፈ በሃገራት ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና አሳድሯል፡፡ በመሆኑም ሀገራት በጤናው፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚ እና ሌሎች ዘርፎች በኩል የተለያዩ የዝግጅት እና የምላሽ ሥራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በተመሳሳይ በሃገራችን የወረርሽኙን ሥርጭት በመግታት በሽታው በህብረተሰቡ ጤናና በሃገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ እርምጃዎችን መንግስት በሽታው ወደ ሃገር መግባቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ አንስቶ ሲወስድ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ተደርጓል፣ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉባቸው የህዝብ ስብሰባዎች ታግደዋል፣ ከውጭ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ መንገደኞች በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ ውስጥ እንዲቆዩ ተደርጓል፡፡ እነዚህን እርምጃዎች በተሟላ መልኩ ማስፈጸም እንዲቻልም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅና አስፈጻሚ ግብረ-ሃይል በማቋቋም ወረርሽኙን ለመከላከል ከፍተኛ ርብርብ ሲያደረግ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በ 2012 ሊደረግ ታስቦ የነበረው ሃገራዊ ምርጫም ለበሽታው ሥርጭት መስፋፋት ሊያደርስ የሚችለውን ተጽዕኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሰፊ ጥናትና የባለሙያዎች ምክክር ከተደረገ በኋላ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት እንዲራዘም ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የጤና ሚኒስቴር ወረርሽኙ ያለበትን ሁኔታ እንዲሁም በመንግስት በኩል በጊዜ የተወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ በየጊዜው ጥናት እያጠናና በሃገር ውስጥ እዲሁም በውጭ

ሃገር ያሉ ባለሙያዎችን እያማከረ፣ የሃገራትን ተሞክሮና የዓለማቀፍ ተቋማትን ምክር ከግምት ውስጥ ያስገባ ምክረ-ሃሳብ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት ይታወቃል።

በዚህም መሰረት ወረርሽኙ በሃገራችን ውስጥ እስከ አሁን ካሳየው ባህርይ አንጻር በቀጣይ ሊፈጠር የሚችለውን አጠቃላይ ባህርይ አስመልክቶ የተሠሩ ትንበያዎችን፣ በሽታውን ለመቆጣጠር የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም ያስከተሉትን እና ወደፊት ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች አጠቃላይ ሪፖርት እና እነዚህን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግና የባለሙያዎች አማካሪ ካውንስል በማማከር የተዘጋጁ ምክረ ሃሳቦችን አቀርባለሁ።

## *በኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአሁኑ ወቅት የሚገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ*

የ ኮቪድ-19 በሽታ በሃገራችን ውስጥ ወደ ሁሉም ክልሎች የተሰራጨ ሲሆን እንከ አሁን ድረስ በሁሉም  ዞኖችና ከ 900 በላይ ወረዳዎች ውስጥ ተከስቷል። ከዚህ በተጨማሪ አሳሳቢ በሆነ መልኩ የጉዞም ታሪክ ሆነ ከታመመ ሰው ጋር ንክኪ የሌላቸው የኮቪድ-19 ታማሚዎች በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ተገኝተዋል። በአገር አቀፍ ደረጃ፣ የኮቪድ-19 በሽታ ከተገኘባቸው ውስጥ 95 በመቶ የታወቀ የጉዞ ታሪክ በሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ የተከሰተ ስርጭት ነው(community transmission)። ይህም ደግሞ ወረርሽኙ በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያየ መጠንም ቢሆን እየተስፋፋ መምጣቱን ያሳያል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ መስከረም 6, 2013 ድረስ 1,165,647 የላቦራቶሪ ምርመራ የተደረገ ሲሆን ይህም አገራችን በአጠቃላይ ምርመራ ብዛት ከአፍሪካ 3ኛ እንዲሁም ደግሞ የምርመራ ብዛት ከእያንዳንዱ 1 ሚሊየን ህዝብ አንፃር 22ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ደረጃ  ካላቸው አገራት አንፃር ሲታይ አፈፃፀሙ ጥሩ የሚባል ነው። ለአብነት ያህል ናይጄሪያ 39ኛ እና ግብፅ 41ኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአሁኑ ወቅት የሚገኝበት አጠቃላይ ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል፦

- በኢትዮጵያ እስከ መስከረም 6 ከተደረገው ምርመራ ውስጥ 66,224 ሰዎች (5.7%) በበሽታው እንደተያዙ የተረጋገጠ ሲሆን 58 በመቶ ያህሉ በአዲስ አበባ ሲሆን ቀሪው ከፍተኛ ቁጥር በኦሮሚያ፣ትግራይ እና አማራ ክልል ይገኛል።

- 62 በመቶው ወንዶች ሲሆኑ 38 በመቶው ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡
- 78 በመቶው ህሙማን በላቦራቶሪ ምርመራ ወቅት የበሽታው ምልክትም ሆነ ህመም አልታየባቸውም፡፡
- 86 በመቶ የበሽታው የተገኘባቸው ከ15-59 ባለው የእድሜ ክልል ሲሆኑ ከ25 ዓመት በታች ያሉት የህብረተሰብ ክፍሎች 30 በመቶ ይይዛሉ፡፡
- እስከ መስከረም 6, 2013 ድረስ 1045 ሰዎች (1.6%ቱ) ለሞት የተዳረጉ ሲሆን በጤና ተቋምት ህክምና አገልግሎት ካገኙ 33,207 ታካሚዎች ውስጥ 26,665 (80%) የሚያህሉት ከበሽታው አገግመዋል፡፡ በተጭማሪም15,088 ሰዎች የቤት ውስጥ ክትትልና ክብክቤ ማግኘት ችለዋል፡፡፡ በአሁኑ ሰአት ቫይረሱ ካለባቸው ውስጥ ወደ 7 ሺህ የሚደርሱ ሰዎች ህክምና ማዕከላት ውስጥ ይገኛሉ፡፡
- ከ60 ዓመት በላይ የእድሜ ክልል ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በሽታው ከተገኘባቸው ሰዎች ውስጥ 7 በመቶ ቢሆኑም ከሞት አንፃር ግን 53 በመቶውን ይይዛሉ፡፡

አንድ ግለሰብ በበሽታው መያዙን የምናረጋግጥበት እስከ አሁን ሲሰራ ከነበረው እና ናሙናን ከአፍ እና አፍንጫ በመውሰድ ከሚደረገው የላቦራቶሪ ምርመራ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ከዚህ ቀደም በበሽታው ተይዘው የነበሩ ሰዎችን ለማወቅ የሚሰራ የአንቲቦዲ የደም ምርመራም በ14 ከተሞች ላይ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት ለዚህ በሽታ ተጋልጠው የነበሩ ሰዎች ሰውነታቸው በሽታውን ለመቋቋም የሚያመርተውን አንቲቦዲ (antibody) በደም ውስጥ በመርመር ወረርሽኙ ምን ያህል እንደተስፋፋ ለማወቅ ተጨማሪ መረጃን ማግኘት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ዳሰሳ መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ የበሽታው ክስተት በአማካይ 4.5 % ሲሆን ይህ ግን ከክልል ክልል እና ከከተማ ከተማ የተለያየ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በአዲስ አበባ የበሽታው ክስተት በአማካይ 4.1% ሲሆን በሌሎች ክልሎች ደግሞ ከዚህ የሚበልጥ ሥርጭት ተመዝግቧል (ጋምቤላ ከተማ= 9.3%፣ ድሬደዋ ከተማ=7.7%፣ጅግጅጋ= 7.5% እና ሀረሪ ከተማ=5.5%)፡፡ በመሆኑም ከዚህ ዳሰሳ ለመረዳት እንደሚቻለው በጥናቱ በተካተቱት 14 ከተሞች ውስጥ የበሽታው ሥርጭት በማህበረሰቡ ውስጥ መኖሩን ነው፡፡

## *አገር አቀፍ የማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ እና ምርመራ( ማንም) ዘመቻ*

የኮቪድ ወረርሽኝን ስርጭት በተሻለ ለመረዳትና ለመቆጣጠር፤ በቀጥተኛና በተዘዋዋሪ በበሽታው ጉዳት የደረሰባቸውን ለመታደግ እና መሰረታዊ የጤና፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ

አገልግሎቶችን ለማስቀጠል ያስችል ዘንድ ከነሀሴ 1 እስከ 30 ድረስ የዘለቀ አገር አቀፍ የማህበረሰብ ንቅናቄ እና ምርመራን ዘመቻ የተከናወነ ሲሆን ዘመቻውም የሚከተሉትን ውጤቶች አስገኝቷል፡፡

- ባሳለፍነው አንድ ወር ውስጥ፣ በመላ አገሪቱ 8 ሚሊዮን ቤቶች ተጎብኝተው፣ ለነዋሪዎቹ አስፈላጊ የሆኑ መልእክቶች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ለበሽታው ተጋላጭ ሰዎች መለየት ተችሏል
- በህትመት ውጤቶች አማካይነት ከ12 ሚሊዮን ለሚበልጡ ሰዎች የጤና መልእክቶችን እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ከ40 ሚሊዮን ለሚበልጡ ወገኖች መልእክት በማድረስ፣ ባህሪያቸውን እንዲለውጡ፣ በሽታውን ለመከላከል ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምክር ተለግሷል፡፡
- ወረርሽኙን ለመከላከል ከሚረዱ መንገዶች አንዱና ዋነኛው ማስክን መጠቀም እንደመሆኑ መጠን፣ “ማስክ ኢትዮጵያ” የሚል ንቅናቄ በማስጀመር ዘመቻው በሁሉም ክልሎች እና የመስተዳደር ከተሞች ሊባል በሚችል ደረጃ ተካሂዷል፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ በማረሚያ ቤቶች፣የተፈናቃይና የስደተኞች ካምፕና በመሳሰሉት ቦታዎች በሚገኙ ሰዎች ላይ በማተኮር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን፣ የማስተማር እና በተወሰነ መልኩ የምርመራ ስራ መስራት ተችሏል፡፡
- በነሀሴ ወር ውስጥ በእድሜ የገፉ እና ከፍተኛ ተጋላጭነት አላቸው በሚባሉ ወገኖች ላይ በማተኮር በአጠቃላይ 575 ሺ ሰው በማንም ዘመቻ መመርመር የተቻለ ሲሆን ይህም በሽታው ከተገኘበት ጊዜ አንስቶ የተመረመረውን ሰው ቁጥር ከእጥፍ በላይ አሳድጓል፡፡
- ከዘመቻው በፊት በቫይረሱ የተያዘው ሰው ቁጥር 20,924 የነበረ ሲሆን በነሐሴ ወር ብቻ በቫይረሱ እንደተያዙ የታወቀው የሰው ቁጥር 37,748 ነበር፡፡ ይህም እስካሁን በሽታው ከተገኘባቸው ወደ 64 ከመቶ የሚሆነው የተገኘው በነሐሴ ወር ውስጥ ነበር ማለት ነው፡፡
- የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን መከላከሉ እንዲህ በተጠናከረ ሁኔታ በአገር አቀፍ ደረጃ ሲከናወን ሌሎች መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶቻችን እንዳይስተጓጎሉ ጥረት ተደርጓል፡፡
- በዘመቻው የኮቪድ 19 የበሽታ ስርጭት በተሻለ ከማወቅ በተጨማሪ የመከላከልና የመቆጣጠር አቅምን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ተቸሏል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መግለፅ ይቻላል

- በየደረጃው የአመራሩን ትኩረት ከማግኘት አንፃር ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፣
- በመገናኛ ብዙሃን(ሚዲያ) እና ሌሎች ስራዎች ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን ተከናውነዋል፣
- የቅኝት ስራ ለመስራት የሚያስፈልጉ አደረጃጀቶች በስፋት ማደራጀት ተችሏል፡፡ ከ10,500 በላይ የድንገተኛ ምላሽና የበሽታ ቅኝት የሚያከናውኑ ቡድኖች ማደራጀት ተችሏል፣
- የላበራቶሪ ናሙና መሰብሰቢያ ቦታዎችን በየወረዳው ማስፋት ተችሏል
- የምርመራ አቅም በከፍተኛ ደረጃ አድጓል፡፡ በነሃሴ ወር በቀን በአማካይ 19 ሺ ምርመራ ማከናወን ተችሏል ፣
- በጤና ተቋማትና የአልጋ ቁጥር ማሳደግና የቤት ውስጥ ህክምና አገልግሎት ማስጀመር ችለናል

## የቀጣይ ወራት ትንበያ

የጤና ሚኒስቴር ከተለያዩ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ ባሉ የዘርፉ ባለሙያዎች የተለያዩ ዘዴዎችን (methodologies) በመጠቀም የትንበያ ሞዴሎችን የሰራን ሲሆን፣ ከሳይንሳዊ ትንበያዎች እንደምንረዳው በበሽታው የሚዘውን የሰዎች ቁጥር፣ የሞት ቁጥርና ወረርሽኙ ከፍተኛው ቁጥር/ጣሪያ (peak) የሚደርስበት ጊዜ በዋናነት የሚወሰነው በአካለዊ መራራቅና፣ በተለይ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል የሚተገበርበት ደረጃ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አካላዊ ርቀት 25 በመቶና የአፍና አፍንጫ 50 በመቶ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ መተግበር ከተቻለ ምንም አይነት እርምጃ ባይወሰድ ሊደርስ ከሚችለው የበሽታ ስርጭትና ሞት አንፃር፣ በ92 በመቶ መቀነስ እንደሚቻል ያሳያል፡፡ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭንብልና ሁሉም እንዲጠቀም ማድረግ ከተቻለ ድግሞ ስርጭቱን በከፍተኛ መጥን መቀነስና ወረርሽኙ ከፍተኛው ቁጥር/ጣሪያ (peak) የሚደርስበት ጊዜ በማራቅ፣ የሞት መጠንን በእጅጉ ከመቀነሱም በላይ በጤናው ስርዓት፣በማህበራዊ፣ኢኮኖሚና በፖለቲካ ዘርፍ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ይቻላል፡፡

ምንም እነኳን እነዚህ የትንበያ ልምምዶች ወደፊት ሊኖር የሚችለውን ክስተት ለመረዳት ጠቃሚ ቢሆኑም፤ እርግጠኛ ባልሆኑ ታሳቢዎች (Assumptions) ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ እንዲሁም በሽታው አዲስ ከመሆኑ አንጻር የስርጭት ባህሪውና የሚያስከትለው

ተጽዕኖ ላይ ያለው ዕውቀት ምሉዕ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በበሽታው የሚያዘውን የሰዎች ቁጥር፣ የሞት ቁጥር፣ ወረርሽኙ ከፍተኛው ቁጥር/ጣሪያ (peak) የሚደርስበት ጊዜ ፣ ሊያደርስ የሚችለው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጫና በዋናነት የሚወሰነው በሽታውን ለመከላከል እንደመንግስትና ህዝብ በምንወስደው ቁርጠኝነት ነው፡፡

## ወረርሽኙን ለመከላከል በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች

በሽታው እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31 ቀን 2019 በቻይና ሁቤ ግዛት ውሃን ከተማ መከሰቱ ሪፖርት ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ  አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅትና የመከላከል ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት የድንገተኛ ህብረተሰብ ጤና አደጋዎች አለርት መልዕክት እንደደረሰ፡-

- ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ.ም፣ የድንገተኛ ህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ዝግጁነትና ምላሽ ቡድኖች ተደራጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ተደርጓል፣
- ጥር 18 ቀን 2012 ዓ.ም. የድንገተኛ ህብረተሰብ ጤና አደጋ ኦፕሬሽን ማዕከል ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፤  በሃገር መውጫና መግቢያ በሮች ላይ በተለይም በቦሌ ዓለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሙቀት ለኬትና ልየታ ስራ ተጀምሯል፣
- የካቲት 21 ቀን 2012 ዓ.ም. የብሄራዊ ሚኒስተሮች ኮሚቴ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ተቋቁሟል፣
- መጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም. የመጀመሪያው የኮቪድ-19 ታማሚ ተለይቷል፣
- መጋቢት 7 ቀን 2012 ዓ.ም. የመጀመሪያው ዙር እርምጃዎች ተወስደዋል (ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል፣ ህዝባዊ ስብሰባዎች ታግደዋል፣ የአካላዊ መራራቅ እርጃዎች ተወስደዋል)፣
- መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም.  ወደ ሃገር ቤት የሚመጡ መንገደኞች 14 ቀናት አስገዳጅ የለይቶ ማቆያ ውስጥ እንዲቆዩ ተወስኗል እንዲሁም
- መጋቢት 30 ቀን 2012 ዓ.ም. አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ እስከ ነሀሴ 30 ተግባራዊ ሆኗል፡፡

መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በየደረጃው የሚያስፈጽምና በአጠቃላይ የወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር ሥራውን ማስተባበር የሚችል አደረጃጀት በመፍጠር ይህንን አደገኛ ወረርሽኝ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት በርካታ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያሉት የሚኒስትሮች

ኮሚቴ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ንዑስ ኮሚቴዎቹን ለመጥቀስ፡

- ሀብት ማሰባሰብ ንዑስ ኮሚቴ
- ለይቶ ማቆያ ቦታዎች ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ
- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ንዑስ ኮሚቴ
- የኮሚዩኒኬሽን ንዑስ ኮሚቴ
- የጤና ንዑስ ኮሚቴ
- ማክሮ ኢኮኖሚ ንዑስ ኮሚቴ
- ደህንነት እና ህግ ማስከበር ንዑስ ኮሚቴ
- የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ንዑስ ኮሚቴ
- የውጪ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ
- የለይቶ ማቆያ አስተዳደር ንዑስ ኮሚቴ
- የቀብር አስፈፃሚ ንዑስ ኮሚቴ

በክልል ደረጃ በርዕሰ መስተዳደሮች/ በምክትል ርዕሰ መስተዳደሮች የሚመሩ ግብረኃይሎች ተቋቁመው ምላሹን እየመሩ ይገኛሉ፡፡ በጤናው ዘርፍ በኢትዮጲያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና በተመሳሳዩ በየክልሉ በርካታ ንዑሳን ቡድኖች ያሉት የድንገተኛ ህብረተሰብ ጤና አደጋ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል፤ በጤና ሚኒስቴር ንዑሳን ቡድኖች ያሉት የኮቪድ አስተባባሪ ግብረ ሀይል፤ እንዲሁም ንዑሳን ኮሚቴዎች ያሉት የባለሙያዎች አማካሪ ካውንስል በማቋቋም ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መታወጁ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በአፍና አፍንጫ መሸፈኛ አጠቃቀም፣ በአካላዊ ርቀት እና የእጅ ንጽህና አጠባበቅ ልምድ ላይ መሻሻሎችን ያመጣ ከመሆኑም በተጨማሪ፤ የትራንስፖርት ተጠቃሚዎችን በ 50 በመቶ በመቀነሱ ፣ ጭፈራ ቤቶች እና መጠጥ ቤቶች በመዝጋቱ፣ የስፖርት ሁነቶችን በማስቀረቱና እንዲሁም በኃይማኖት ተቋማትና በሃይማኖት በአላት ወቅት ሊኖር የሚችለውን ከፍተኛ ሥርጭት በከፊል ማስቀረት በመቻሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በተጨማሪም በህብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ለማቃለል እዲቻል ለስጋት ተጋላጭ የሆኑ አቅመ ደካሞችን ለማገዝ የሚያስችሉ አደረጀጀቶች

በመንግስትና በህብረተሰቡ ጥረት ተፈጥሯል፡፡ በእነዚህ አደረጃጀቶች በኩል የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፣ የአልኮል ሳኒታይዘርና ሌሎች የመከላከያ ቁሳቁስ እንዲሁም የምግብ እና የህክምና ቁሳቁስ ድጋፍ በየአካባቢው ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም በህብረተሰቡና በመንግስት ትብብር የምግብ ባንኮች ተቋቁመዋል፡፡

በዘርፈ ብዙ ምላሽ በኩልም በተለይ ጤና ሚኒስቴር ፤ ሰላም ሚኒስቴር፤ ትራንስፖርት ሚኒስቴር፤ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ፤ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ፤ ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር፤ አደጋ ስጋት መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፤ አየር ማንገድ፤ ክልልና ከተማ መስተዳድሮች፤ የፌደራልና የክልል ፖሊስ እና ሌሎች በመቀናጀት የተመላሾች፤ የመንገደኞች እና የረጅም ርቀትና ድንበር ተሻጋሪ ጭነት መኪና አሽከርካሪዎችን እንዲሁም የትምህርት ዘርፍም ትምህርት ቤቶችንና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ወደ ጊዜያዊ ለይቶ ማቆያነት በመቀየር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒሰቴር እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የሃገር ውስጥ አምራቾችንና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ያካተቱ በተለይም ለኮቪድ መከላከልና መቆጣጠር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲያመርቱ በማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

በመሆኑም መንግስት አስፈላጊ የሚባሉ እርምጃዎችን ፈጥኖ የወሰደ ሲሆን የመከላከል ሥራዎችንም ለማስፈጸም እና ለመከታተል ይረዳ ዘንድ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የሚመሩ መዋቅሮችን አቋቁሟል፡፡ እንደ “Our World in Data” የተሰኘ ዓለም አቀፍ መረጃ ተንታኝ ተቋም የኮቪድ-19ን ወረርሽኝ ለመግታት ሀገራት የወሰዱትን እርምጃዎች ምን ያህል ጥብቅ መሆናቸውን የገመገመ ሲሆን በዚህም መሰረት ከ100% (በጣም ጥብቅ) ኢትዮጵያ በሚያዚያ ወር መጀመሪያ ላይ 80% ያስመዘገበች ሲሆን በዚህ ሁኔታ እስከ ሰኔ ቆይቶ በሰኔ ወር አራተኛ ሳምንት ውስጥ ወደ 70% ዝቅ ብሏል፡፡ በነሀሴ ወር አጋማሽ ግን ተሻሽሎ 78% የደረሰ ሲሆን ይህም እንደ “Our World in Data” ግምገማ ላምሳሌ ከኬኒያ፣ ሱዳን፣ ግብፅ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ እና ጋና ሲነጻጸር የኢትዮጵያ ውጤት የተሻለ ሲሆን አንዳንድ ሀገራት ደግሞ ከኢትዮጵያ የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

## *በጤናው በኩል የተሰሩ የዝግጅት እና ምላሽ ስራዎች*

በጤናው ግብረ ሀይል ከተሰሩት ዋና ዋና የቅድመ ዝግጅትና የምላሽ ስራዎች መካከል የሚከተሉት ናቸው፦

## እቅድና ትንበያ

ወቅቱን ያገናዘበ የአደጋ ጊዜ ቅድመዝግጅትና ምላሽ እቅድ እንዲሁም የትንበያ በሶስት ዙር ተሰርቷል።

## የላብራቶሪ ምርመራ

በየደረጃው ያለውን የምርመራ አቅም ከማጠናከር አንጻር ምርመራ የሚሰጥባቸውን ላብራቶሪዎች ቁጥር ምንም ካልለበረበትና ወደ ውጪ ልኮ ከማስመርመር ተነስቶ ወደ 54 ላቦራቶሪዎች ማሳደግ የተቻለ ሲሆን ከመጋቢት እስከ መስከረም ባለው ጊዜ በ24 ሰዓት የሚሰራውን የምርመራ መጠን ከ 50 ወደ 19000 ምርመራ ማሳደግ ተችሏል። የምርመራ አቅምን አሁንም በቀጣይ ለማሳደግ በተለይ የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ እየተሰራ ሲሆን፤ በሀገር ውስጥ የምርመራ ኪቶችን ከቻይና ድርጅትና መንግስት ጋር በመተባባር ማምረት ጀመረናል።

## ሃብት ማሰባሰብና ማከፋፈል

ለጠንካራ ምላሽ 360 ሚሊየን የኣሜሪካ ዶላር እንደሚያስፈልግ የተለየ ሲሆን ከአለምአቀፍ አጋር ድርጅቶችና የግሉን ሴክተር ጨምሮ ከሌሎች አካላት ለጤናው ምላሽ 122,246,628.70 ዶላር የተሰበሰበ ሲሆን ከመንግስት 3.9 ቢልየን ብር (109,109,807.97 ዶላር) መመደብ ተችሏል::

በግዢና በእርዳታ 1,003,257,460 ብር የሚያወጡ ለህክምና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች/ግብዓቶች፤ እንደ የኦክስጂን ሲሊንደሮችን፣ የበሽተኛ አልጋዎችን፣ እና ቬንትሌተሮችን የመሳሰሉ የህክምና መሳሪያዎች የላቦራቶሪ ግብዓቶች ለክልል እና ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ተሰራጭቷል። በተጨማሪ የወረርሽኙን መስፋፋት ለመግታትና የጤና ባለሞያዎችና ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ በዕርዳታና በግዢ የተገኙ 823 ሚልየን ብር የሚገመቱ የራስን መጠበቂያ/መከላከያ እና የፅዳት ቁሳቁሶች በተለያየ ዙር ተሰራጭተዋል። በጥሬ ገንዘብም ለሁሉም ክልሎች እስከአሁን በአራት ዙር የ1,494,320,717 (1.5 ቢልዮን) ብር ድጋፍ ተደርጓል።

## የሰው ሃብት ማጠናከር

- ከ3900 በላይ ባለሞያዎች ደፌደራልና በክልል ተቀጥረው እንዲሰማሩ ተደርጓል

- ከቀይ መስቀል ማህበር ጋር በመተባበር 15000 የበጎ ፈቃደኞች በየክልሉ እንዲሰማሩ ተደርጓል
- በኮቪድ ስራ የተሰማሩ የጤና ባለሙያዎችና ሰራተኞች የጤና መድህን ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል
- ከ14800 በላይ የጤና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል

## ድጋፍና ክትትል

- በጤና ሚኒስቴር ክልሎችን የሚደግፍ ቡድን ተቋቁሞ በተለያየ ዙር ክልሎች ጋር እዚያው ሆነው አብሮ በመስራት ሲደግፉ ቆይተዋል፡፡
- ከኮቪድ ጎን ለጎን ሌሎች መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶች እንዳይጎዱ በኮቪድ ወቅት የሌሎች አገልግሎቶች ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ የአተገባባር መመሪያ በመቅረጽና በማውረድ በየሳምንቱም በሚሰበሰቡ መረጃዎች ጠንካራ ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ሶስት ዙር ድጋፋዊ ምልከታ ተደርጓል በዚህም ሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች፣ 91 ዞኖች፣ 381 ወረዳዎች 1031 የጤና ተቋማት ተጎብኝተዋል
- ከክልል የጤና ቢሮ ሀላፊዎች ጋር የጤና ሚ/ር አመራርና ግብረሀይሉ ያለማቋረጥ ሳምንታዊ የኦንላይን ውይይትና ክትትል ይደረጋል፡፡

## የህክምና እና የለይቶ ማቆያ ተቋማት ዝግጁነት

ለኮቪድ 19 ምላሽ ከተሰሩ ስራዎች ውስጥ ዋነኛው የሆነው እና አሁንም ተጠናክሮ እየቀጠለ የሚገኘው የህክምና እና የጊዜያዊ ለይቶ ማቆያ ማዕከላትን በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀት እንቅስቃሴ ነው፡፡ በመሆኑም የህክምና አቅምን ከማሳደግ አንጻር 16,289 ሰዎችን መያዝ የሚችሉ የለይቶ ማቆያዎችን፣ 21,280 የህክምና አልጋዎችን እንዲሁም 653 የጽኑ ህሙማን ህክምና አልጋዎችን የያዙ የህክምና ማዕከላት ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን፣ በቅርቡ ከአሜሪካ መንግስት የተገኙትን ጨምሮ 523 አርቴፍሻል የመተንፈሻ ማሽኖችን (ቬንቲሌተሮች) ዝግጁ ማድረግ ተችሏል፡፡

በግል ዘርፉ በኩል ደግሞ የግል የጤና ተቋማት ከወረርሽኙ ምላሽ አንጻር ሊጫወቱ የሚችሉትን ከፍተኛ ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት እነዚህ ተቋማት በቂ የሆነ ዝግጁነት ይኖራቸው ዘንድ ለማገዝ  የግል ተቋማትን ተደራሽ የሚያደረግ የጋራ መድረክ ተመቻችቷል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ በሚገኙ 21 ሆስፒታሎች እና 34 የጤና ማዕከላት ላይ ዳሰሳ

ተደርጎ በጋራ የዝግጁነት እና ምላሽ እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን ከ50 በላይ ከሆኑ የጤና ተቋማት ለተወጣጡ 192 የጤና ባለሞያዎች ደግሞ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ 30 የግል ተቋማት ለኮቪድ 19 ምርመራ የሚሆኑ ናሙናዎችን እየወሰዱ ወደላቦራቶሪ የሚልኩ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ የሚገኝ አንድ የግል ምርመራ ማዕከል እና አንድ የግል ሆስፒታል ደግሞ የኮቪድ 19 ምርመራን እያካሄደ ይገኛል፡፡ ሌሎችም ዝግጅት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ አበባ የሚገኙ ሁለት የግል ሆስፒታሎች ለኮቪድ 19 ታማሚዎች የህክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በሁሉም ክልሎች የግል ተቋማት ለኮቪድ 19 ታማሚዎች የህክምና አገልግሎት ወደ መስጠት እንዲገቡ የሚያስችል ፕሮቶኮል ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ውሏል፡፡

## *ዘርፈ-ብዙ የምላሽ ስራዎች*

ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሁሉን ተደራሽ ያደረገ ምላሽ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የተለያዩ ሴክተሮች አብሮ መስራትን የሚጠይቅ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ዘርፈ-ብዙ የሆነ ምላሽን ከመስጠት አንጻር ሰፊ የሆኑ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ ስራዎች ውስጥ አንደኛው በተለያዩ ምክንያቶች በከፍተኛ ሁኔታ ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን (የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ከስደት ተመላሾች፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና የሚያጠቡ እናቶች፣ ህጻናት፣ ተጓዳኝ የጤና እክል ያላባቸው ሰዎች፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን) ከዚህ ወረርሽኝ ለመታደግ የተሰሩ ስራዎችን ያካትታል፡፡ ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን ተግባራት መጥቀስ ይቻላል፦

- በከፍተኛ ሁኔታ ተጋልጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶች፣ ህጻናት፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና የሚያጠቡ እናቶች እና የአካል ጉዳተኞችን) በመለየት ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- በ26 የስደተኞች መጠለያ ካምፖች ውስጥ በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች ላይ የለይቶ ማቆያ ቦታዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እንዲሁም የበሽታ ቅኝት እና የተግባቦት እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡
- ከዚህ ቀደም በተለያየ ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች ለ3 ወር የሚያገለግሉ የአደጋ ጊዜ መድኃኒቶች እና የህክምና ቁሳቁሶች ተልከዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ያለንክኪ የሚሰሩ የሙቀት መለኪያዎች ለተለያዩ የስደተኞች መጠለያ ካምፖች ተሰራጭተዋል፡፡

- በአስራ አንድ የለይቶ ማቆያ ማዕከላት የአካል ጉዳኞችን ፍላጎት ምን ያህል ባገናዘበ መልኩ እየሰሩ እንደሆነ ለማየት የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ያሉት ችግሮች ተለይተው ወጥተዋል።
- በአንዳንድ ማረሚያ ቤቶች የህክምና፡ የለይቶ ማቆያና ማግለያ ቦታዎች እንዲዘጋጁና ግብዓት እንዲሟላ ተደርጓል።
- ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በተሽከርካሪዎች መዉጫና መግቢያ ኬላዎች ላይ መኪናዎችን የመርጨትና ሾፌሮችንና ረዳቶቻቸውን የመመርመር ስራ ተከናዉኗል።

## ወረርሽኙ ያስከተለው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጫና

የ ኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሃገራችን ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እቅስቃሴ ላይ መጠነ ሰፊ አሉታዊ ጫና አሰድሯል። ለምሳሌም በማክሮ ኢኮኖሚው ዘርፍ የአጠቃላይ ምርት መጠን መቀነስና፣ የዋጋ ግሽበት ከማስከተሉም በላይ የግል ኢንቨስትመንቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በተጨማሪም የስራ ዕድል ላይ እንዲሁም በገቢና በምጣኔም ላይ ጫና አሳድሯል። በተለይ ከሃገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ድርሻ ባለው በአገልግሎት ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዱ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

በፖለቲካው ዘርፍም ሃገራዊ ምርጫው መራዘሙን መጥቀስ ይቻላል። በማህበራዊና በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ላይም ቀላል የማይባል ጫና ፈጥሯል። በትራንስፖርትና በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የከፋ ጉዳት አድርሷል።

በትምህርቱ ዘርፍ 26 ሚሊዮን ተማሪዎች ከመጋቢት 7 2012 ጀምሮ ከትምህርት ገበታቸው እንዲቀሩ በመደረጉ በተማሪዎች የመማር አቅምና ጥራት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚፈጥር የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ከትምህርት ቤቶች መዘጋት ጋር ተያይዞም ጾታዊ ጥቃትና ያለድሜ ጋብቻ ሪፖርቶች ማሻቀብ ጀምረዋል። በተመሳሳይ ከትምህርት ቤቶች መዘጋት ጋር ተያይዞ የህጻናት ምገባ ፕሮግራሞች መቋረጣቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እደሚችል ይገመታል።

በጤናውም በኩል መደበኛ አገልግሎቶች ላይ ጫና በመፈጠሩና እንዲሁም በማህበረሰቡ ስጋት ምክንያት አገልግሎቶች እንዳይስተጓጎሉ ጥረት ቢደረግም በሚፈለገው መጠን አልነበረም።

## ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች

የኮቪድ-19 በሽታ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም በተተነበየው ደረጃ ህመምና ሞት እያስከተለ ባይሆንም ፤ አሁንም የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ቀላል የማይባል መሆኑና በሁሉም ክልሎች ባሉ ወረዳዎች መዳረሱ ከባድ አደጋ የመፍጠር አቅም እዳለው ያሳያል፡፡ለዚህም እንደማሳያ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

- በሁሉም ክልሎች፣ዞን፣ወረዳዎች (ከ900 ወረዳዎች በላይ) በሚባል ደረጃ ተሰራጭቷል
- በበሽታው የተያዙ ሰዎች፣በፅኑ የታመሙና በበሽታው ህወታቸው ያለፈ ሰዎች ቁጥር በፊት ከነበረው አንጻር ጨምሯል
- ከተገኙት ታማሚዎች ውስጥ 95 በመቶ በማህበረተሰቡ ውስጥ የተከሰተ እና በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኝ ስርጭት መሆኑ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡
- ሳይንሳዊ ትንበያዎች የሚሳዩት ስርጭቱ ገና ጡዘቱ ላይ አለመድረሱና በማህበረሰቡ እንደሚወሰደው የመከላከል እርምጃ የስርጭት መጠን የሚወሰን መሆኑ ነው፡፡

በሌላው ጎን የኮቪድ-19 በሽታ ረዘም ላለ ጊዜ አብሮን ሊቆይ እንደሚችል የዓለም ጤና ድርጅት አሳውቋል፡፡ ምንም እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ክትባቶች በሙከራ ላይ ያሉ እና ጥቂቶቹም አበረታች ደረጃ ላይ መድረሳቸው እና እንደ እኛ ያሉ ሀገራትን ተደራሽ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት አለምአቀፍ ድርጅቶች በጋራ መስራት መጀመራቸው ቢታወቅም ፤ ክትባቱ ከተረጋገጠ በኋላ ተደራሽ ማድረግና በቂ ክትባት በግዢም ሆነ በእርዳታ ማግኘት አሁን ካለው ዓለም አቀፍ እሽቅድምድም አንጻር ቀላል ጉዳይ አይሆንም፡፡ ስለሆነም ቢያንስ ለሚቀጥሉት ጊዚያት በሽታው በሃገራችን የህብረተሰብ ጤና ስጋት ሆኖ ይቀጥላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ተስፋ ሰጪ ሁታዎች አሉ፡፡ አንዱና ዋነኛው አሁን የምንጠቀምባቸው እንደ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ፣ አካላዊ ርቀት መጠበቅና እጅን ቶሎ ቶሎ መታጠብ ያሉ መከላከያ ዘዴዎች በአግባቡ መተግበር ከተቻለ በሽታውን ለመከላከል ውጤታማ እንደሆኑ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተለይ የፊት ጭምብል መጠቀም በሁለም በቀላሉ መተግበር የሚችልና በሽታውን የመከላከል አቅሙ ከሌሎቹ መከላከያ መንገዶች የተሻለ ሊሆን እንደሚችል የሚያመላክት አንድአንድ መረጃዎች ስላሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ አጠናክሮ ከተተገበረ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ይህን ለመደገፍ በሃገር ውስጥ አምራቾችና በኢንዱስትሪውን ዘርፍ የማስክና ሌሎች እንደ ሳኒታይዘር ያሉ ምርቶች በከፍተኛ

ሁኔታ ማደጋቸውና በማህበረሰቡም ያለው ግንዛቤ በሽታው ሲከሰት ከነበረው እጅግ የተሻለ መሆኑ አበረታች ነው፡፡

ከዚሁ ጋር አብሮ መታየት ያለበት በሽታውን ለመቆጣጠር እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች በአጠቃላይ በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እቅስቃሴዎች በተለይ ደግሞ በልማት ሥራዎች ላይ እያሳደሩት ካለው አሉታዊ ተጽዕኖዎች በተጨማሪ በጊዜ ሂደት የጤና ዘርፉ ላይም ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ጫና ማሳደራቸው አይቀሬ ነው፡፡

ስለሆነም የጤና ሚኒስቴር ሁኔታውን በሚኒስቴር መ/ቤቱ፤ በህብረተሰብ ጤና ኢንስቲቱት እና በኮቪድ-19 የባለሙያዎች አማካሪ ካውንስል ሰፊ ውይይት ከተደረገበት በኂላ የሚከተሉትን አጠቃላይና ዝርዝር ምክረ ሃሳቦች አቅርቧል፡፡

1. **አጠቃላይ ምክረ ሃሳብ**

**እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚወሰዱ እርምጃዎች፡** የኮቪድ-19 በሽታን ለመከላከልና ሥርጭቱን ለመግታት እየተተገበሩ ያሉ ክልከላዎችና እገዳዎችን የአነሳስ (easing restrictions) ሁኔታ እንደየአካባቢው የወረርሽኙ ሥርጭት ተጨባጭ ሁኔታ መቃኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በየአካባቢው በጥንቃቄ በሚሰራ የሁኔታ እና የስጋት ዳሰሳ መሰረት ቢተገበር የተሻለ ይሆናል፡፡ ይህ ሂደት ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸውን ወረዳዎችና የህብረተሰብ ክፍሎች ከበሽታው ለመታደግ የሚጠቅም ሲሆን በሽታው መካከለኛና ዝቅተኛ የስጋት መጠን ባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እቅስቃሴውን ለማነቃቃት ይጠቅማል፡፡ ይህ ሂደት ማህበረሰቡን ያሳተፈና የማህበረሰብ ባለቤትነትን ያረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ ክልከላዎች እንደ አስፈላጊነቱ ቢነሱም ቀጣዩን ጊዜ ወረርሽኙን ለመከላከል የሚደረጉ እርምጃዎች ለማስተግበርና በየደረጃው የሚሠሩ ተግባራትን ለማስፈጸም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ ቶሎ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ለሚደረገው እንቅስቃሴ ቁልፍ ነው፡፡

**የጤና ሥርዓቱን ዝግጁነት ማጠናከር፡** እስከ አሁን የጤናውን ስርዓት ለማጠናከር የተሰራው ሰፊ ስራ ያለውን ዝግጁነት እጅግ ያጠናከረ ሲሆን፡ ለቀጣዩ ወቅት በየደረጃው ያለውን የጤና ሥርዓት በበጀት፣ በሰው ሃይል፣ በማቴሪያልና በመረጃ ሥርዓት በከፍተኛ ሁኔታ ማጠናከር ሊቀጥል ይገባል፡፡ የሰው ሃይሉን ዝግጁ ሆኖ እንዲቆይ ከማድረግ በተጨማሪ የበጎ ፍቃደኞችን፣ የማህበረሰብ ጤና ሠራተኞችን እና ሌሎችንም አጋዥ ሃይሎች በሙሉ አቅም

አሟጦ መጠቀም የሚያስችል ዝግጁነት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በግብዓት የተሟሉ የህክምና ተቋማትን ማስፋት፣ ለለይቶ ማቆያና ለህክምና መስጫነት ጥቅም ላይ ሲውሉ የነበሩ የትምህርት ተቋማት ተለዋጭ ማዕከላት ማዘጋጀት፣ የድንገተኛ ህብረተሰብ ጤና ስጋትና አደጋዎች አለርት ሥርዓት፣ የቤት ለቤት ጉብኝትና እዲሁም የፈጣን መረጃ ልውውጥ ሥርዓትን ማጠናከር የሚቀጥል ይሆናል፡፡ እያደገ ያለው የምርመራ አቅም አሁንም በቀጣይ ማሳደግ ቁለፍ ሲሆን በሀገር ውስጥ መመረት የተጀመሩት የምርመራ ኪቶች ለዚህ አጋዥ ይሆናሉ፡፡

**በሥራና አገልግሎት መስጫ አካባቢ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን መጨመርና ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፡** በሥራ ላይ ሆነው ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑ ሠራኞችን ለመጠበቅና በርካታ ሰዎች አገልግሎት የሚያገኙባቸው ተቋማት የበሽታው ሥርጭት ማዕከል እዳይሆኑ ለመከላከል፤ በሥራ አካባቢ የኮቪድ-19 ቅድመ ጥንቃቄዎች በሁሉም ጊዜ፣ የተቀመጠውን መስፈርት በጠበቀ መልኩ መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የሌሎች ሃገራት ተሞክሮ እደሚያሳየውም በምግብ ቤቶች፣ በሆቴሎች እንዲሁም የህዝብ አልግሎት በሚሰጥባቸው የመንግስትና የግል ተቋማት የማስክና የአካላዊ ርቀት ድንጋጌዎች በጥብቅ መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በተለይ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ መጠቀም በሁሉም የአገራችን ክፍል አስገዳጅ ማድረግና አፍፃፀሙ ላይ ባለቤትነትን መፍጠርና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ሙሉ ለሙሉ ለማስቀጠል የሚጠቅም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

**በየደረጃው ያለውን የአመራር ቁርጠኝነትን ማጠናከር**፡ እየጨመረ ያለውን የበሽታው ሥርጭት መግታት የሚቻለው ሁሉም አካለት በባለቤትነትና በቅንጅት ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ቀን ከለሊት መሥራት ሲችሉ ብቻ ነው (Whole of Society Whole of Government Approach)፡፡ በተለይም የኮቪድ-19 ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚደረጉ የክልከላ እና እገዳ ማሻሻያዎች የበሽታው ሥርጭት እንዳይጨምር ከመቸውም ጊዜ በላይ የሁሉንም ንቁ ተሳትፎ እና ቅንጅታዊ አሠራር ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም የማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ እና ምርመራ ዘመቻ የፈጠረውን ተነሳሽነት ሳይቋረጥ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ብሄራዊ ግብረኃይሉ የክልል ግብረኃይሉን ቢያንስ በየ15 ቀኑ መገምገም አለበት፡፡ እንዲሁም በየደረጃው ያለው የፖለቲካ አመራር በየሳምንቱ ኮቪድን ለመከላከልና ለመቆጣጠርና የሚከናወኑ ተግባራትን መደግፍና መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ባለድራሻ አካላት ( የመንግስትና የግል) የኮቪድ 19 የመከላከልና የመቆጣጠር ስራን እንደ አንድ ዋና ተግባራቸው

አካተው እንዲሰሩ ማደረግና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት( Mainstreaming COVID 19 response in all relevant sectors) ያስፈልጋል፡፡

2. **ዝርዝር ምክረ-ሃሳቦች**

**የህግ ማዕቀፍ በተመለከተ**

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ከማስተግበር አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ይታመናል፡፡ አሁን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ማለቁን ተከትሎ እና ኢኮኖሚያዊ ፤ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ከላይ በዘረዘርነው መልኩ እንዲቀጥሉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤ ይህ ሲደረግ  የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች የጤና ሚኒስቴርና የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከዚህ ቀደም በህግ በተሰጣቸው ስልጣን ተግባራዊ በማድረግ የመከላከል ስራውን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

**ትምህርት ቤቶችን ስለመክፈት**

የኮሮና ቫይረስ አለማቀፍ ወረርሽኝ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የተሰሩ በርካታ ጥናቶች እንሚያመለክቱት በሽታው በህጻናት ላይ ያለው ቀጥተኛ ተፅዕኖ ውሱን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በትምህርት ላይ ያሉ ህጻናትና ወጣቶች በበሽታው የመያዝና በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ ዝንባሌያቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ ህጻናት በሽታውን ከትምህት ቤት ይዘው ወደ ቤት በመመለስ በእድሜ ወደገፉና ተዛማጅ በሽታዎች ወዳሉባቸው የቤተሰብ ክፍሎች የማስተላለፍ  ዕድላቸው ሰፊ በመሆኑ ትምህርት ቤቶች የወረርሽኙን  ስርጭት ሊያባብሱ እንሚችሉ በመገመት በርካታ ሃገራት ትምህርት ቤቶቻቸውን ዘግተዋል፡፡

ስለሆነም ትምህር ቤቶችን መልሶ ስለመክፈት ሲታሰብ፣ አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ በሽታው እንዳይዘው የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን፣ ከትምህር ቤት ወደ ቤት በሚጓዝበት ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች፣ እንዲሁም በቤት ውስጥ ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑ የቤተሰብ አባላትን ከመጠበቅ አንጻር የሚሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ  ፓኬጅ ሊተገበር ይገባል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የመንግስት፤ የማህበረሰቡ፣ የወላጆች፣  የመምህራንና የተማሪዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በአብዛኛው የአለማችን ክፍሎች ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶች የተዘጉ ሲሆን በዚህም ደግሞ ከ1.8 ቢሊየን ተማሪዎች ቤት ለመቆየት ተገደዋል፡፡ እንደየሀገራቱ የወረርሽኝ ሂደት ደግሞ የተለያዩ ሀገራት ትምህርት ቤችን መልሰው ከፍተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ እንደ ዴንማርክ፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድ፣ የካናዳዋ ኪዩቤክ ግዛት እና አንድአንድ የእስራኤል ትምህርት ቤቶች ከሚያዝያ 7 (April 15) በኋላ ትምህርት ቤቶቻቸውን መልሰው ከፍተዋል፡፡ እነዚህ ሀገራት ትምህርት ቤቶቻቸውን በከፊልም ሆነ በሙሉ በሚከፍቱበት ጊዜ የነበራቸው የስርጭት መጠን ሲታይ እለት ተእለት የነበረው የታማሚ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ማሻቀብ ያቆመበት እና ወረርሽኑ በአንጻሩ የተረጋጋበት ወቅት ላይ ነበር፡፡ የአከፋፈት ሂደት ላይ የተለያዩ ሀገራት የተለያየ ስልትን ተጠቅመዋል፡፡ ትምህርት ቤቶችን መልሰው ከከፈቱ በኋላ በተከሰተ የወረርሽኝ ስርጭት ለጥንቃቄ ሲባል መልሰው የዘጉ ሀገራትም ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ደቡብ ኮሪያና ሆንግ ኮንግ ትምህርት ቤቶቻቸውን ከከፈቱ በኋላ ተቆጣጥረውት የነበረው ወረርሽኝ ማህበረሰቡ ውስጥ መልሶ ማንሰራራት በመጀመሩ፤ ምንም እንኳ በትምህርት ቤቶቻቸው ውስጥ ወረርሽኑ ባይከሰትም ለጥንቃቄ በሚል መልሰው ዘግተዋል፡፡

ከአፍሪካ ሀገራት እንደ የደቡብ አፍሪካ፣ ካሜሮን እና ታንዛንያ ያሉ ሀገራት ትምህርት ቤችን መልሰው የከፈቱ ሲሆን በደቡብ አፍሪካ ትምህርት ቤቶች ከተከፈቱ በኋላ በመምህራን እና ተማሪዎች ላይ የበሽታው ስርጭት በጨመሩ ከ25,762 ትምህር ቤቶች ውስጥ 968ቱ መልሰው እንዲዘጉ ሆኗል፡፡

ከነዚህ አገራት የምንረዳው ትምህርት ማስጀመር ከስጋት ሙሉ ለሙሉ ነጻ መሆን ባይችልም አከፋፈት ሂደቱ ከፍተኛ ጥንቃቄና ዝግጅት እንደሚፈልግ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ተብለው በአለም የጤና ድርጅት (WHO) ከተቀመጡ መስፈርቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል:-

- እስከአሁን ባለው ሁኔታ የኮሮና በሽታ ህጻናትን ምን ያህል እንደሚያጠቃ እና ህጻናት በሽታውን በምን ያህል እንደሚያስተላልፉ ያለው መረጃ
- ትምህርት ቤቶች ባሉበት አካባቢ ያለው የበሽታው ስርጭት
- የትምህርት ቤቶች ሁኔታ እና የኮቪድ-19 በሽታን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ያላቸው አቅም

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና መስፈርቶች መሰረት አስፍላጊውን ቅድመ ጥንቃቄዎች ባሟላ ሁኔታ ትምህርት ቤቶችን እንደየ አካባቢው የበሽታ ሥርጭት ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ መክፈት ይቻላል። የኮቪድ 19 በሽታን ለመከላከል ከሚወሰዱ ርምጃዎች ውስጥ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው እጅና ፊትን አዘውትሮ መታጠብና አካላዊ ርቀት ሲሆኑ ከዚህ አንፃር በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ካሉ ተቋማት ቀላል የማይባል ቁጥር በቂ የውሃ አቅርቦት፣ የንፅህናና መሰረተ ልማት የሌላቸው በመሆኑና በሀገር አቀፍ ደረጃ አማካይ የተማሪ ክፍል ጥምርታ 1፡56 መሆኑ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚኖራቸውን አቅም አነስተኛ ያደርገዋል። በመሆኑም ትምህርት ቤቶች ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ መልሶ ለመክፈት ከትምህርትና ጤና ሴክተር በተጨማሪ የብዙ ሴክተሮች (የውሃ፣መስኖ እና ኤሌክትሪክ፤ የትራንስፖርት፣ የሴቶች ህጻናት እና ወጣቶች፣ የሰላም ሚ/ር፣ ወዘተ) ተሳትፎ እና በዘርፎቻቸውም ድርሻቸውን መወጣት ይጠይቃል።ትምህርት ቤት መጀመር ከመወሰኑ በፊት ጠንካራ ግብረሃይል በየደረጃው ተቋቁሞ ወደስራ መግባት አለበት። በተጨማሪም በተለያዩ ትምህርት ቤቶችና ዩንቨርስቲዎች ያሉትን የኳራንቲን፣ የለይቶ ማቆና የህክምና ማዕከላትን ተለዋጭ ቦታ ማመቻቸት ያስፈልጋል (ለዚህም አስፈላጊውን በጀት መመደብ ያስፈልጋል)።

ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን የኮቪድ ወረርሽኝ ስጋት በቀነሰ መልኩ ለመክፈት ሊተገበሩ ከሚገባቸው የዝጅግት ስራዎች ውስጥ ከዚህ በታች የተገለጹት ይገኙበታል፡-

- የበሽታው ስርጭት በአንፃራዊ ዝቅተኛ በሆነባቸው አከባቢዎች መጀመርና ቀስበቀስ ወደ ሌሎች አከባቢ ማስፋት
- ደረጃ በደረጃ ትምህርት ቤቶችን መክፈት፤ የተወሰኑ የትምህርት ክፍሎችን መክፈትና የበሽታውን ሁኔታ እያዩ ቀስበቀስ ሌሎች ክፍሎችን ማስጀመር፣
- የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛዎችን ማድረግ፣
- የውሃና የሳሙና አቅርቦት ማረጋገጥ፣
- የወላጆች፣አስተማሪዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካለትን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣
- በአንድ ክፍል ውስጥ ያለውን የተማሪ ብዛት መቀነስ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መተግበር፣ ለምሳሌ፡- የፈረቃ ትምህርት ለተወሰነ ጊዜ ማስጀመር፣
- መስኮቶችንና በሮችን ሁልጊዜ ክፍት ማድረግ፣
- አካለዊ ቅርርብን ሊቀንሱ የሚችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችና ሎሎች የመከላከያ ዘደዎችን መተግበር ያስፈልጋል።

**የህዝብ መሰባሰቦችንና ኢኮኖሚያዊና ማክበራዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ**

የሰዎችን ስብስብ የሚጠይቁ የተለያዩ ተግባራትንና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ መፍቀድ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም የሰዎች ቁጥር በመመጠንና በተጨማሪ መሰረታዊ የኮቪድ-19 መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዶችም እንደሚፈፀሙ ታሳቢ በማድረግ (በቂ አየር ዝውውር፣ 2 ሜትር አካላዊ መራራቅ መጠበቅ፣ አስገዳጅ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ መጠቀም፣ የእጅ መታጠብና ሌሎች እንደዘርፉ ሁኔት ሊተገበሩ የሚችሉ የመከላከያ ዘዴዎች) ስብሰባና ስልጠናዎች፤ የሃይማኖት ስነስርዓቶች፤ ካፌ፤ ምግብ ቤቶችና ሆቴሎች፤ የቱሪስቶች መዳረሻዎች፤ሲኒማ፣ትያትር ቤቶች የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች፤ቀብሮች፤ ስፖርታዊ ውድድሮች፤ የግብይት ሁኔታ፤ የአደባባይ በዓላት የመሳሰሉት ሁኔታዎች ከኮቪድ መከላከል ጋር የሚካሄዱበት ዝርዝር ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ቅድም በጠቀስኩት መመሪያ የሚወጣና የሚተገበር ይሆናል፡፡

**ሃገራዊ ምርጫ ስለማካሄድ**

በኮቪድ ወረሽኝ ምክንያት የተለያዩ ሀገራት ምርጫን በከፊልም ሆነ በሙሉ ላልተወሰነ ጊዜ ያራዘሙ ሲሆን አንድ አንድ ሀገራት ደግሞ ምርጫዎቻቸውን ቀድሞ በተያዘላቸው መርሀግብር መሰረት ወይንም በአዲስ ቀነ-ቀጠሮ አከናውነዋል፡፡ ከአፍሪካ ውጭ ባሉ ሀገራት ላይ በርቀት ድምጽን የመስጠት ሂደት በይበልጥ የተለመደ ከመሆኑ እና ካለው የመገናኛ ብዙሀን ተደራሽነት አንጻር ምርጫዎች ተካሂደዋል ወይንም ለመካሄድ ዕቅድ ተይዟል፡፡ ነገር ግን በተለያዩ አፍሪካ ሀገራት ላይም ቢሆን ምርጫዎች በኮሮና ወቅት የተደረጉባቸው አጋጣሚዎች ሲኖሩ እነዚህም ሀገራት ምርጫን ባካሄዱበት ወቅት የነበረው የወረርሽኝ ሁኔታ እና ኮቪድን ከመከላከል አንጻር ያደረጓቸው ዝግጅቶች በጥቂቱ ለማጥቀስ፤

ከአፍሪካ ማሊ፣ ቤኒን፣ ብሩንዲ፣ ጊኒ እና ማላዊ የኮቪድ በሽታ በሀገራቱ ከተከሰተ በኋላ ምርጫዎችን አካሂደዋል፡፡ ከማላዊ ውጭ እነዚህን ሀገራት የሚያመሳስላቸው ሁሉም ምርጫቸውን ያካሄዱት ወረርሽኙ ገና ሳይስፋፋ በፊት ሲሆን በማላዊ ግን ምርጫው ሲካሄድ 1300 በላይ ታማሚዎች ተመዝግበው ነበር፡፡

በሀገራችን ወረርሺኙ አሁንም የጤና ስጋት ቢሆንም ቀደም ሲል ከነበሩት ትንበያዎች አንጻር ከፍተኛ አለመሆኑ፤ ኮቪድ-19 በሽታ ረዘም ላለ ጊዜ አብሮን ሊቆይ የሚችል መሆኑና በአንፃራዊ በአሁኑ ሰዓት ምርጫው ሲራዘም ከነበርንበት ሁኔታ ስለስረጭቱ የተሸለ መረጃ ያለን

በመሆኑ ፤ ቀደም ሲል ከነበረበት በተሻለ የመከላከል ሁኔታዎች መኖሩ (በሽታውን ለመከላከል የሚረዱ ሳይነሳዊ መረጃ (evidences) መገኘት ለምሳሌ የእጅ ንጸህና መጠበቅና የፊት ማስክ መጠቀም ስርጨቱን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንሱት መታወቁ፣ የህብረተሰቡ ግንዛቤ መሻሻል ለአብነት የፊት ማስክ የመጠቀም ባህል በአዲስ አበባ 75 በመቶ መድረሱ፤ የማስክ፤ ሳኒታይዘር ምርት በአገር ውስጥ በስፋት መኖሩ፤ የጤና ተቋማት ዝግጁነትና ግብዓት አቅርቦት መሻሻል፤ የምርመራ ኪት ማምረትን ጨምሮ የላቦራቶሪ አቅም ማደግ እና የዘርፈብዙ ምላሽ በተሻለ ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ እና የሀገራትን የምርጫ ተሞክሮም በማየት፣ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ሃገራዊ ምርጫውን ማካሄድ ይቻላል፡፡

- ከዚህ በፊት ከነበረው የምርጫ ሂደት በተለየ መልኩ ኮቪድ-19ኝ መከላከልን ከግምት ውስጥ ያስገባ የምርጫ ስነ-ምግባር፣ ደንብ እና ማስፈጸሚያ መመሪያዎችና ማዘጋጀትና በተዘጋጁት ዝርዝሮች መሰረት በሁሉም ደረጃ በበቂ ዝግጅቶች ወደ ትግበራ መግባት ያስፈልጋል፡፡
- በዚህ ሂደት ውስጥ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የወረርሽኝ ሥርጭት ከተከሰተ በተለየ ሁኔታ መታየት ሊያስፈልገው እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

# አመሰግናለሁ!